የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ—ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 15
ADDIS ABABA–31st January, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፰/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፯፻፪

## CONTENTS

Proclamation No. 268/2002
Water Resources Development Fund Establishment and its administration Proclamation ........ Page 1702

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፰/፲፱፻፺፬
### የውሃ ልማት ፈንድ ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የውሃ አቅርቦትንና የሳኒቴሽን አገልግሎትን ማጎልበትና ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፣

በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የመስኖ እርሻ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት አንዱ በመሆኑ ለልማቱ መስፋፋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

እነዚህንም ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነውን ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማእከል በማሰባሰብ ሁሉም ፍትሐዊና ርትአዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አሠራር መቀየስ ተገቢና ለዚሁም የውሃ ልማት ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፰/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

### *PROCLAMATION No. 268/2002*
### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE WATER RESOURCES DEVELOPMENT FUND AND ITS ADMINISTRATION*

WHEREAS, in order to enable the population to be beneficiary of reliable and sustainable water supply and sanitation services it is necessary to enhance and strengthen water supply and sanitation services;

WHEREAS, in the course of the development efforts to ensure food self sufficiency irrigated agriculture being one of the activities which deserves particular attention it is necessary to create the conducive conditions for its development;

WHEREAS, it is proper to centralize the money collected from various sources to implement the above objectives and to create ways and means whereby everyone may benefit from it fairly and equitably, it is necessary to establish a water resources development fund;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Republic of Ethioia, it is hereby proclaimed as follows:

### *PART ONE*
### General

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Water Resources Development Fund Establishment and its Administration Proclamation No. 268/2002."

2. *Definitions*
Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

፩· «የውሃ ልማት» ማለት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የመስኖ ልማት እና የሳኒቴሽን አገልግሎት ነው፣

፪· «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፤

፫· «ሳኒቴሽን» ማለት ከመኖሪያ ቤት ፣ ከኢንዱስትሪ ፣ ከንግድና ከመሳሰሉት ተቋማትሚወጣን ፍሳሽ አሰባስቦ በማጣራት ተገቢውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ ውሃ ማስገኘት ነው፣

፬· «የመስኖ ልማት» ማለት ማንኛውም ለእርሻና ለግጦሽ የሚውል መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ነው፣

፭· «የውሃ አቅርቦት" ማለት ለመጠጥና ለሌሎች ግልጋሎቶች የሚውል ደረጃውን የጠበቀ የተጣራ ውሃ ነው፤

፮· «ቦርድ» ማለት የውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ ነው፣

፯· «ተቋም» ማለት የመንግሥት የከተማ መጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲሁም በተደራጁ ገበሬዎች የሚለማ መስኖ ነው፣

፰· «ሚኒስትር» እና «ሚኒስቴር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የውሃ ሀብት ሚኒስትር እና ሚኒስቴር ነው።

## ክፍት ሁለት
## ስለፈንዱ መቋቋም

፫· *መቋቋም*

፩· የውሃ ልማት ፈንድ /ከዚህ በኋላ «ፈንዱ» እየተባለ የሚጠራ/በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለዚህ አዋጅ ዓላማ ማስፈጸሚያ ይውላል።

፬· *የፈንዱ ዓላማ*

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩· በውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው ለሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የውሃ አቅርቦት አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፣

፪· የመስኖ ልማትን በማስፋፋትና ዘለቄታዊነቱን በማረጋገጥ በምግብ ራስን ለመቻል ለሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስቻል፣

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱትን ዓላማዎች እውን ለማድረግ ወጪን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሠረተ የረዥም ጊዜ ብድር ለመስጠት ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

፭· *የፈንዱ ምንጮች*

፩· ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፣

ሀ) ከፈንዱ ዓላማ ጋር በተያያዘ ከውጭ መንግሥታት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብ እርዳታና ብድር፣

ለ) ከፌዴራል መንግሥት ከሚመደብለት በጀት፣

ሐ) ከልዩ ልዩ ምንጮች።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ገንዘብ ለፈንዱ ሲባል በጽሕፈት ቤቱ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሣብ በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተቀማጭ ይደረጋል። ጽሕፈት ቤቱ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ ሊኖረው ይችላል።

፫· መንግሥት በብድር በሚያገኘው ገንዘብ ላይ ከአበዳሪው ወገን ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ከሚጣል ወለድ በስተቀር ተጨማሪ ወለድ አይጥልም።

፮· *ስለሚለቀቀው ገንዘብ*

በፀደቀው ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለሚከናወኑ ሥራዎች ከፈንዱ ሂሣብ ገንዘብ ወጭ ሆኖ የሚለቀቀው የገንዘብ ብድር መጠን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

1) ''Water Resources Development'' means for the purposes of this Proclamation irrigation, water supply and sanitation services;
2) ''Region'' means a region designated by Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia including, for the purposes of this Proclamation the Administrations of Addis Ababa and Dire Dawa;
3) ''Sanitation'' means to obtain water which conform with acceptable quality standard by treating sewage emanating from house holds, industries, commercial undertakings and from similar other undertakings;
4) ''Irrigation'' means any irrigation development that enable someone to cultivate land for farming and grazing purposes;
5) ''Water Supply'' means treated water of acceptable standard used for drinking and other uses;
6) ''Board'' means the Water Resources Development Fund Board;
7) ''Institution'' means government urban water supply service providers and organized farmers engaged on irrigation development;
8) ''Minister'' and ''Ministry'' means the Ministry and Minister of Water Resources, respectively.

## *PART TWO*
## Establishment of the Fund

3. *Establishment*
   1) There is hereby established the Water Resources Development Fund (hereinafter "the Fund'').
   2) The Fund shall be a permanent source of finance and shall be used to implement the objectives of this Proclamation.

4. *Objectives*

   The Fund shall have the following objectives:
   1) to enable institutions which are engaged in the provision of water supply and sanitation services to be fully self sufficient in the provision of reliable and sustainable water supply service to the community;
   2) to make significant contribution in the course of development efforts directed towards attaining food self sufficiency by expanding and ensuring the sustainability of irrigation development:
   3) to create favourable conditions for the realization of the objectives mentioned in Sub-Articles (1)and (2) of this Article and thereby grant long term loans on the basis of the principle of cost recover.

5. *Sources of the Fund*
   1) The Fund shall be collected from the following sources:
      (a) grants and loans from foreign governments and international donor agencies made in connection with the objectives of the fund;
      (b) budgetary allocations by the Federal Government;
      (c) from other sources.
   2) The money mentioned in Sub-Article (1) of this Article shall be deposited in the bank account opened in the name of the Office for the purpose of the Fund by the Ministry of Finance and Economic Development. The office may have a foreign exchange bank account.
   3) The government shall not impose any other additional interest except the interest to be imposed on the basis of the agreement made with lending partners.

6. *Release of Money*

   Release of money out of the Fund account shall be effected on the basis of the approved annual work programme according to the directives issued by the Board.

፯· በፈንዱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች
   ፩· በፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆን ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆን አለበት።
   ፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው በተጨማሪም በአንቀጽ ፲፬(፬) መሠረት በቦርዱ የሚወጡ መመዘኛዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፰· ስለፈንዱ ሂሣብ
   ፩· ጽሕፈት ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብት በተለይ ይይዛል።
   ፪· የፈንዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው ይመረመራሉ። የኦዲተሩ የምርመራ ውጤት የበጀት ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባል።

ክፍል ሦስት

ስለፈንዱ አስተዳደር

፱· የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት መቋቋም
   ፩· የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት /ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ/ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
   ፪· ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል።

፲· ዋና መሥሪያ ቤት
የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ፣ እንደአስፈላጊነቱ በሃገሪቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል።

፲፩· የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር
ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣
   ፩· የቦርዱን ውሣኔዎችንና መመሪያዎችን በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
   ፪· የፈንዱን ሂሣብና ሪኮርድ ይይዛል፣
   ፫· የቦርዱን ሥራ አመራር የስብሰባ ሪኮርዶችን ይይዛል፣
   ፬· በየዓመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገምና ቦርዱ በሚያወጣው የብድር አሰጣጥ አወሳሰን መመዘኛ መሠረት ቅደም ተከተል በማውጣት ከፈንዱ በብድር ይሰጣል፣
   ፭· ለፈንዱ መግባት የሚገባውን የብድር ተመላሽ እና በአንቀጽ ፭ ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኘውን ተሰብሳቢ ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ ይሰበስባል፣ በፈንዱ ሂሣብ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
   ፮· ፈንዱን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሣቦችን ለቦርዱ ያቀርባል፣
   ፯· የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

፲፪· የጽሕፈት ቤቱ አቋም
ጽሕፈት ቤቱ፣
   ፩· የውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ፣
   ፪· በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እና
   ፫· አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

፲፫· ስለቦርድ አባላት
ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፲፬· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር
ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣
   ፩· ፈንዱን በበላይነት ያስተዳድራል፣
   ፪· ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣
   ፫· ለፈንዱ መግባት ያለባቸው ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን እና በፈንዱ ሂሣብ መግባታቸውን ያረጋግጣል፣
   ፬· የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የብድር አሰጣጥ አወሳሰን መመዘኛዎችን ያወጣል፣
   ፭· የፈንዱን ኦዲት በኦዲት ሪፖርቶች ይገመግማል፣ በሪፖርቶቹ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፣ በኦዲተር የተመረመረው ዓመታዊው የፈንዱ ሂሣብ እንዲጠናቀርና ይፋ እንዲሆን ያስደርጋል፣



7. *Criteria for being Eligible to be beneficiary of the Fund*
   1) Any beneficiary institution of the Fund shall bear legal personality.
   2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article the criterion laid down under Article 14 (4) by the Board shall be implemented.

8. *Account of the Fund*
   1) The Office shall keep accurate and complete book of account in respect of the account of the Fund.
   2) The books of account and financial documents of the Fund shall be audited annually by the Auditor General or by other auditors designated by the Auditor General. The audit report shall be submitted to the board within six months of the completion of the fiscal year.

*PART THREE*

*Administration of the Fund*

9. Establishment of the Office of the Fund
   1) There is hereby established the Water Resources Development Fund Office (herein after "the Office") having its own legal personality.
   2) The Office shall be accountable to the Minister.

10. *Head Office*
The Fund shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere in the country as may be necessary.

11. *Powers and Duties of the Office*
The Office shall have the followng powers and duties to:
   1) follow up and ensure the proper implementation of decisions and directives of the Board:
   2) Maintain the accounts and records of the Fund;
   3) keep all records of meetings of the Board;
   4) grant loans out of the Fund by evaluating the annually submitted requests and by setting priorities on the basis of the criteria established by the Board for granting loans;
   5) make timely collection of repayment of loans and all money to be collected from sources mentioned under Article 5, and follow up and ensure its entry in the account of the Fund;
   6) submit policy recommendations to the Board regarding the Fund;
   7) own property, enter into contracts and sue and be sued in its own name.

12. *Organization of the Office*
The Office shall have:
   1) Water Resources Development Fund Board;
   2) A General Manager to be appointed by the Government upon the recommendation of the Board; and
   3) The necessary staff.

13. *Members of the Board*
Members of the Board, including the Chairman thereof, shall be designated by the government with their number to be determined as may be necessary.

14. *Powers and Duties of the Board*
The Board shall have the powers and duties to:
   1) administer the Fund;
   2) issue directives on the procedure of collection of the Fund and withdrawal and payments of money from the Fund;
   3) ensure the timely collection of money due to the Fund and their entry in the account of the Fund;
   4) without prejudice to Article 7 of this Proclamation, set criteria for granting of loans;
   5) evaluate the audit report of the fund; ensure that adequate measures are taken in accordance with audit reports and shall see to it that the audited annual reports are completed and made public;

፮· ፈንዱ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል፤
፯· ከፈንዱ ጋር በተያያዘ ዓመታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
፰· የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ይመረምራል፤ ለመንግሥት አቅርቦ ያስፀድቃል፤
፱· የጽሕፈት ቤቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ለመንግሥት በማቅረብ ያሾማል።

**፲፭· የቦርዱ ስብሰባዎች**

፩· የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ ይደረጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
፪· በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
፫· የቦርዱ ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ ነው። ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፲፮· የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

፩· የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ያቅዳል፤ ይመራል፤
፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር ሳይወሰን፣ ዋና ሥራ አስኪያጁ፤
  ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤
  ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማዎች በመከተል ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤
  ሐ) የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
  መ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
  ሠ) በጽሕፈት ቤቱ ደረጃ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤
  ረ) ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
፫· ሥራ አስኪያጁ ለጽሕፈት ቤቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

**፲፯· በጀት**

፩· የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፤
፪· የጽሕፈት ቤቱ የበጀት ዓመት ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል።

**፲፰· ስለሂሣብ መዛግብት አያያዝ**

፩· ጽሕፈት ቤቱ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር ይይዛል።
፪· የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው ይመረመራሉ። የኦዲተሩ የምርመራ ውጤት የበጀት ዓመት ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ይቀርባል።

6) seek ways and means for the growth of the Fund;
7) advise the government on policy issues related to the Fund.
8) review the annual work programme and budget of the office and submit to the government for approval;
9) recommend the General Manager of the Office for appointment by the government.

15. *Meetings of the Board*

1) The Board shall have regular meetings every three months, provided however, extra ordinary meetings of the Board may be held at any time when called by the Chairman.
2) The quorum shall be constituted by the presence of more than half of the members.
3) All decisions shall be made by a majority vote of those present. In case of a tie the chairman shall have a casting vote.
4) The Board may, without prejudice to the provison of this article, adopt its own rules of procedure

16. *Powers and Duties of the General Manager*

1) The General Manager shall, in accordance with the general directives issued by the Board, plan, direct and administer the activities of the office.
2) without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the General Manager of the Office shall:
   (a) exercise the powers and duties of the office specified under Article 11 of this Proclamation;
   (b) employ and administer the employees of the office in accordance with directives to be issued by the Board following the basic priniciples of the Federal Civil Service Law;
   (c) prepare and submit to the Board the annual budget and work program of the office, implement same upon approval;
   (d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the office;
   (e) represent the office in all its dealings with third parties;
   (f) perform such other duties as may be given to him by the Board.
3) The General Manager may delegate part of his powers and duties to the employees of the office to the extent necessary for the effective performance of the activities of the office.

17. *Budget*

1) The budget of the office shall be allocated by the Government;
2) The fiscal year of the Fund shall commence on the 1st day of Hamle and shall end on the 30th day of Sene.

18. *Books of Account*

1) The Office shall keep accurate and complete books of accounts with supporting documents.
2) The books of accounts and other financial documents of the office shall be audited annually by the Auditor General or by the person designated by him. The result of the Audit report shall be presented to the Board within six months following the end of the fiscal year.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**
ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገገባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፳. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**
ይህ አዋጅ ከጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## PART FOUR
## *Miscellaneous Provisions*

*19. Inapplicable Laws*
No law shall, in so far it is inconsistent with this Proclamatin, have force or effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

*20. Effective Date*
This Proclamation shall enter into force as of the 31st day of January, 2002.

Done at Addis Ababa, this 31st day of January, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE